- እግዚአብሔር እጅግ ስለተቆጣ ሰይጣንን ከመንግሥተ ሰማይ አባረረው።

- እግዚአብሔር ክፉ የሚሠራ ማንም ከእርሱ ጋር እንዲኖር አይፈቅድም።

- ሰይጣን በእግዚአብሔር ላይ ያነሣውን ዐመፅ የተከተሉ ብዙ መላእክት ከእርሱ ጋር ነበሩ።

- ሰይጣንን የተከተሉ መላእክት በእርሱ ላይ ስላመጹ፥ እግዚአብሔር ስማቸውን ለወጠ።

- ሰይጣንን የተከተሉት መላእክት አዲሱ ስማቸው ማን ነው?

- አጋንንት።

- አጋንንት የእግዚአብሔር ጠላቶች ናቸው።

- አጋንንት የሁሉም ሰው ጠላቶች ናቸው።

- ሰይጣንን የተከተሉትን አጋንንት እግዚአብሔር በምን ቀጣቸው?

- እግዚአብሔር እጅግ ስለተቆጣ ሁሉንም ከመንግሥተ ሰማይ አባረራቸው።

- እግዚአብሔር ክፉ የሚሠራ ማንም ከእርሱ ጋር እንዲኖር አይፈቅድም።

- እግዚአብሔር ሰይጣንና አጋንንቱን የቀጣቸው በሌላ በምንድን ነው?



## ትምህርት 4

1. እግዚአብሔር ሥጋ ወይም አጥንት ወይም ደም አለው?

ሀ- የለውም።

2. እግዚአብሔር ሥጋ ወይም አጥንት ወይም ደም ከሌለው ታዲያ እግዚአብሔር ምንድን ነው?

ሀ- እግዚአብሔር መንፈስ ነው።

3. እግዚአብሔር የት ነው ያለው?

ሀ- እግዚአብሔር ሁል ጊዜ በሁሉም ቦታ አለ።

4. ከእግዚአብሔር ለመደበቅ ወዴት መሄድ እንችላለን?

ሀ- ከእግዚአብሔር ልንደበቅ አንችልም።

5. ስንት እግዚአብሔር አለ?

ሀ- አንድ እግዚአብሔር ብቻ ነው ያለው።

6. አንድ እግዚአብሔር የሆኑት ሦስቱ አካላት እነማን ናቸው?

ሀ- እግዚአብሔር አብ እግዚአብሔር ወልድና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ነው።

- መላእክት ከየት መጡ?

- በመጀመሪያ ሁሉንም መላእክት የፈጠራቸው እግዚአብሔር ነው።

- ከመጀመሪያው በፊት የትኛዎቹም መላእክት አልነበሩም።

- እግዚአብሔር ከመላእክት የሚበልጠው እንዴት ነው።

- ምክንያቱም እግዚአብሔር ከመላእክት በፊት ስለ ነበረ ነው።

- መላእክትን የፈጠረው እርሱ ስለሆነ ነው።

- ለመላእክት ሕይወትን የሰጣቸውም እግዚአብሔር ስስለሆነ ነው።
- እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ስለሆነ ነው።

- እግዚአብሔር መላእክትን የፈጠራቸው ደምና ሥጋ እንዲኖራቸው አድርጎ ነው?

- አይደለም።
- እግዚአብሔር መላእክትን የፈጠራቸው መናፍስት አድርጎ ነው።

- እግዚአብሔር መንፈስ ነው መላእክትም መናፍስት ናቸው፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ከመላእክት ይበልጣል።

- እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው።
- ነገር ግን መላእክት ሁሉን ቻይ አይደሉም።

- እግዚአብሔር ሁል ጊዜ በሁሉም ስፍራ መሆን ይችላል።

- ነገር ግን መላእክት በአንድ ጊዜ መገኘት የሚችሉት በአንድ ቦታ ብቻ ነው።

- ምንም እንኳን እግዚአብሔር መላእክቱን መንፈስ አድርጎ ቢፈጥራቸውም አንዳንድ ጊዜ ሰውን ለመምሰል ውጫዊውን መልካቸውን ይቀይራሉ።



- አንድ ቀን ደካማና የማይረባ ልጅ አባቱን ከሥልጣኑ ሊያወርደው ተነሣ።

- ታዲያ ያ ጠቢብና ኃያል የሆነው ሹም ልጁ ከሥልጣኑ እንዲያወርደው ይፈቅድለታል?

- በፍጹም አይፈቅድለትም።

- ከእግዚአብሔር ይልቅ ብርቱ ማን ነው?
- ማንም የለም።

- ከእግዚአብሔር ይልቅ ጠቢብ ማን ነው?
- ማንም የለም።

- ሉሲፈር ከዙፋኑ እንዲያወርደው እግዚአብሔር ፈቀደለት?
- አልፈቀደለትም።

- ሉሲፈር ኃጢአት በመሥራት የመጀመሪያ ስለነበረ፤ እግዚአብሔር የሉሲፈርን ስም ለወጠው።

- የሉሲፈር አዲሱ ስም ማን ነው?
- ሰይጣን ነው።

- ሰይጣን ማለት ምን ማለት ነው?
- ሰይጣን ማለት «ጠላት» ማለት ነው።

- ሰይጣን የእግዚአብሔር ጠላት ነው።
- ሰይጣን የሁሉም ሰው ጠላት ነው።

- እግዚአብሔር ሰይጣንን ስለ ክፉ ሥራው በምን ቀጣው?

- ሉሲፈር ምን ሆነ?

- ሉሲፈር የራሱን ጥበብና ውበት ተመለከቶ ታበየ።
- ሉሲፈር ታበየ እግዚአብሔርንም ከዙፋኑ ሊያወርደው ፈለገ።

- ሉሲፈር ታበየ የእግዚአብሔርን ቦታ ለመውሰድ ፈለገ።
- ሉሲፈር ታበየ እግዚአብሔር ለመሆን ፈለገ።

- ሉሲፈር ታበየ ክፉ በመሥራትም የመጀመሪያ ሆነ።

- ክፉ በመሥራት የመጀመሪያ ማን ነበር?
- ሉሲፈር ነበር።

- ክፋት ምንድን ነው?

- እግዚአብሔር የማይፈልገው ማንኛውም ነገር ክፋት ነው።
- እግዚአብሔር የማይፈልገው ሁሉም ነገር ክፋት ነው።

- ሉሲፈር ከዙፋኑ ሊያወርደው እንደፈለገ እግዚአብሔር ያውቅ ነበር?

- አዎን ያውቅ ነበር።
- እግዚአብሔር ሉሲፈር ሊያደርግ የፈለገውን ሁሉ ያውቅ ነበር።

- ሉሲፈር ከዙፋኑ እንዲያወርደው እግዚአብሔር ፈቀደለት?

- አንድ ምሳሌ ልንገራችሁ፡-

- ጠቢብና ኃያል የሆነ አንድ ሹም ነበር።



- እግዚአብሔር መላእክትን የፈጠራቸው ለምንድን ነው?

- እግዚአብሔር ርዳታ ያስፈልገዋል?
- በፍጹም አያስፈልገውም።

- የእግዚአብሔር ኃይል አያልቅም ዘላለማዊም ነው።

- ታዲያ እግዚአብሔር መላእክትን ለምን ፈጠራቸው?

- እግዚአብሔር መላእክትን የፈጠራቸው እንዲወዱት ነው።
- እግዚአብሔር መላእክትን የፈጠራቸው እንዲታዘዙለት ነው።
- እግዚአብሔር መላእክትን የፈጠራቸው እንዲያገለግሉት ነው።

- አንድ ሰው ቤት ከሠራ የዚያ ቤት ባለቤት ማን ነው?
- ቤቱን የሠራው ሰው ነው።

- ለምን?
- ቤቱን የሠራው እርሱ ስለሆነ።

- አንዲት ሴት ማሠሮ ከሠራች የማሰሮው ባለቤት ማን ነው?
- ማሠሮውን የሠራችው ሴት ነች።

- ለምን?
- ማሠሮውን የሠራቸው እርሷ ስለሆነች።

- እግዚአብሔር መላእክትን ከፈጠራቸው መላእክቱ የማን ናችው?
- የእግዚአብሔር።

- ለምን?

- መላእክቱን የፈጠራቸው እግዚአብሔር ስለሆነ።

- እግዚአብሔር መላእክቱን ስለ ፈጠራቸው መላእክት የእርሱ ናቸው።
- እግዚአብሔር መላእክቱን የፈጠራቸው መልካም ወይስ ክፉ አድርጎ ነው?

- እግዚአብሔር መላእክትን የፈጠራቸው መልካም ብቻ አድርጎ ነው።
- እግዚአብሔር መላእክትን ክፉ አድርጎ አልፈጠረም።

- እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ክፉ አድርጎ አልፈጠረም።

- እግዚአብሔር የሚያስበው ሁሉ መልካም ብቻ ነው።
- እግዚአብሔር የሚናገረው ሁሉ መልካም ብቻ ነው።
- እግዚአብሔር የሚያደርገው ሁሉ መልካም ብቻ ነው።

- እግዚአብሔር የፈጠራቸው መላእክት ስንት ናቸው?

- እግዚአብሔር የፈጠራቸው መላእክት ብዙ ናቸው ልንቆጥራቸው አንችልም።

- በመጀመሪያ ሁሉም መላእክት የት ነበሩ?
- ከእግዚአብሔር ጋር በመንግሥተ ሰማይ ነበሩ።

- መንግሥተ ሰማይ ምንድን ነው?

- መንግሥት ሰማይ እግዚአብሔር የሚኖርበት ልዩ ቦታ ነው።

- እግዚአብሔር በመንግሥተ ሰማይ ነው እንዲሁም እግዚአብሔር በምድር ላይ በሁሉም ቦታ ነው።

- መንግሥተ ሰማይ የት ነው?



- አናውቅም ነገር ግን መንግሥተ ሰማይ ከጨረቃ ከፀሐይ እና ከክዋክበት ያልፋል።

- እግዚአብሔር አንድን መልአክ ጠቢብና ውብ አድርጎ ፈጠረው።

- እግዚብሔር ጠቢብና ውብ አድርጎ የፈጠረው መልአክ ማን ይባል ነበር?
- ሉሲፈር ይባል ነበር።

- እግዚአብሔር ሉሲፈርን የፈጠረው መልካም ወይስ ክፉ አድርጎ ነው?

- መልካም አድርጎ ነው።

- እግዚአብሔር መላእክትን የፈጠራቸው መልካም አድርጎ ነው።

- እግዚአብሔር መላእክትን ክፉ አድርጎ አልፈጠራቸው።

- እግዚአብሔር ሉሲፈርን የፈጠረው ብዙ ጥበብ ሰጥቶት ነው ቢሆንም ከሁሉም በላይ ጠቢብ እግዚአብሔር ብቻ ነው።

- እግዚአብሔር ሉሲፈርን የፈጠረው ውብ አድርጎ ነው ቢሆንም ከሁሉም በላይ ውብ እግዚአብሔር ብቻ ነው።

- እግዚአብሔር ሉሲፈርን ስለፈጠረው ሉሲፈር የማን መሆን አለበት?

- የእግዚአብሔር።

- እግዚአብሔር ሉሲፈርን ስለ ፈጠረው ሉሲፈር መታዘዝ ያለበት ማንን ነው?

- እግዚአብሔርን ነው።